# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የስራ፣ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

## የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ

## መመሪያ ቁጥር 114/2014

2014

**አዲስ አበባ**

## መግቢያ

የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ፣ የትርጉም አረዳድ እና አተገባበር ላይ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ፈጻሚዎች የግንዛቤ ልዩነት፣የዝግጁነትና የአፈጻጸም ችግር በመኖሩ በሥራ ፈላጊዎችና በኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስትሪዎች ተገቢውን ድጋፍ በሚፈለገው ደረጃ አለመሰጠቱ በዘርፉ እድገት ላይ የሚያስከትለውን ተግዳሮት ለመፍታት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

አገልግሎትን መስጠት የሚገባቸው ተቋማት ከአሁን በፊት የነበሩባቸውን ከአደረጃጀት፣ ከአሰራር፣ ከሠው ኃይል እና ከግብዓት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተቀናጀ ሁኔታ መስጠት እንዲችሉ ለማድረግ ሁሉም ተቋማት አገልግሎቶቻቸውን ተገልጋይ ተኮር ለማድረግና ያስቀመጡትን ግብና ዓላማ ለማሳካት፣ የገቡትን የዜጎች ስምምነት ሰነድ ለማስፈጸም የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ሁሉም የአንድ ማዕከል አገልግሎት ባለድርሻ አካላት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ሥልጣና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (15) መሠረት ለሥራው ቅልጥፍና ሲባል በአንድ ማዕከል የሚሰጡ አግልግሎቶችን በውክልና የሰጡ በመሆኑ በአንድ ማዕከል የሚሰጠውን አግልግሎት አሰጣጥ የሚመራበትን አሰራር መወሰን በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ሥልጣና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 114/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2. **«አስተዳደር»** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. **«ካቢኔ »** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው፤
4. **«ቢሮ»** ማለት የስራ፣ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤
5. **"ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ "**ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞች ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፤
6. **"አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከሰድስት እስከ ሰላሳ ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001 (ሃምሳ ሺህ አንድ) እስከ 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺህ አንድ) እስከ 1,500,000 (አንድ ሚልዮን አምስት መቶ ሺ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፤
7. **«የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ »** ማለት በቢሮው ውስጥ የሚቋቋም እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ኢንዱስትሪዎች ህጋዊነትን ለማስፈን የሚሰጡ አገልግሎቶች፤ መንግስታዊ ድጋፎችና አገልግሎቶች በተቀናጀ መልኩ ከአንድ ስፍራ በአንድ አስተባባሪ አካል ሥር ካሉ አካላት የሚያገኙበት ጣቢያ ነው፤

8. **«የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አደረጃጀት»** ማለት በከተማው አስተዳደር የመጨረሻው እርከን ማለትም በወረዳው ውስጥ የስራ፣ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ነው፤

9. **«አገልግሎት»** ማለት ለተቋማት ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር አንፃር በጥቃቅንና አነስተኛ ለሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች፣ አንቀሳቃሾች፣ ኢንዱስትሪዎች ፍላጎት ለማሟላት ወይም ግዴታዎችን ለመፈፀም ሆነ ለማስፈፀም የሚሰጥ ተግባር ነው፤

10. **«ተገልጋይ"** ማለት በየተቋማት በተደራጁ የስራ ክፍሎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማግኘት ባለው መብት መሰረት አገልግሎት የጠየቀ ወይም የመጠየቅ መብት ያለው ግለሰብ ወይም ድርጅት ወይም ህጋዊ ወኪል ነው፤

11. **"ስራ ፈላጊዎች"** ማለት የመሥራት ፍላጐትና ችሎታ እያላቸው የራሳቸውን ሥራ በመፍጠርም ሆነ በመቀጠር ቋሚ የሥራ መስክ የሌላቸውን፤ በተለያየ የትምህርት ደረጃ የሚገኙ ዜጎች ናቸው፤

12. **"የሥራ ዕድል ፈጠራ"** ማለት የመስራት አቅም እያላቸው በተለያየ ምክንያት ወደ ስራ ያልገቡ ዜጎችን በጊዜያዊ ወይም በቋሚ የስራ ዘርፎች ማሠማራት ነው፤

13. **"መንግስታዊ ድጋፎች"** ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራተጂ መሰረት ለኢንተርፕራይዞች፣ኢንዱስትሪዎች እንደ የዕድገት ደረጃቸው የሚሰጥ መንግስታዊ ድጋፍ ነው ፤

14. **"ባለድርሻ አካላት"** ማለት የቢሮው አጋዥ የሆኑ ተቋማት ናቸው፤

15. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

16. **"ፆታ አገላለፅ"** በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

3. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ለስራ ፈላጊዎችና በቢሮው አገልግሎት በሚሰጡ የከተማ አስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች እንዲሁም አሁን በሥራ ላይ የሚገኙና ወደፊት በሚቋቋሙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመመሪያው ዓላማ እና መርሆዎች

### 4. የመመሪያው ዓላማ

አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በወረዳ ደረጃ ለተገልጋዩ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ፣ ብዙ ውጣ ውረድ የሚጠይቁት ተግባራት በአንድ ስፍራ አግልግሎት በመስጠት ለስራ ፈላጊዎችና ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ አገልግሎቶች ወጪና ጊዜን በመቆጠብ ፈጣንና ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ እና ባለድርሻ አካላትን ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓትን ለማስፈን ነው፡፡

### 5. የመመሪያው መርሆዎች

1. ለስራ ፈላጊ ነዋሪዎች እና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤ የሚሰጡ አገልግሎቶች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችና ስራ ፈላጊዎች ፍላጎት መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ ማስቻል፣
2. ለስራ ፈላጊዎቸና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች  የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ወጪና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ መልኩ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤
3. የአንድ ማዕከሉ አገልግሎት ሰራተኞች የስነ ምግባር መርሆዎችን የተላበሱና ለሚሰጡትም አገልግሎት ኃላፊነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ፤
4. በአንድ ማዕከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች የሴቶችና ወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ማስቻል፣
5. በአንድ ማዕከል አገልግሎት የሚሰጡ አገልግሎቶች ለማን፣ መቼና እንዴት እንደሚሰጥ ለተጠቃሚዎች ግልፅነት የመፍጠርና ልማታዊ አስተሳሰቦችን ማስፈን መርሆዎች አሉት፡፡

## ክፍል ሦስት

## በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ

## ለስራ ፈላጊ ነዋሪዎች እና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

## የሚሰጡ አገልግሎቶች

6. **የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የምክር አገልግሎት መስጠት**

   ለሥራ ፈላጊዎችና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

   1. የቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣
   2. ሞዴል የንግድ ስራ ዕቅድ ማቅረቢያ ቅፅ አዘጋጅቶ የማቅረብ አገልግሎት መስጠት፤
   3. የንግድ ምዝገባና የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚያስችሉ መስፈርቶች ላይ ግንዛቤ መፍጠር፣
   4. የግብር ከፋይነት ምዝገባ ቁጥርና ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶች ላይ ግንዛቤ መፍጠር፤
   5. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም ምክር አገልግሎት መስጠት.
   6. በግብር አዋጆች ፣ ደንቦች እና መመርያዎች ግንዛቤ መፍጠር፣
   7. ለሰልጣኞች የብቃት ምዘና ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚያስችል ግንዛቤ መፍጠር፤
   8. የብድርና ቁጠባ ምክር አገልግሎት መስጠት እና አገልግሎት አማራጮች ላይ ግንዛቤ መፍጠር፤
   9. የመሳሪያ ሊዝ ኪራይ አገልግሎትን በተመለከት ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያሟሉ የምክር አገልግሎት የመስጠት፤
   10. በኢንተርፕራይዞች ፍላጎት የተለዩት የካፒታል ዕቃዎች ከተጠቃሚዎቹ ጋር በመሆን መስፈርታቸውን አዘጋጅቶ መስጠት፤
   11. የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚያስፈልጉ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች እና ስለሚሟሉበት ሁኔታ ግንዛቤ መስጠት፤
   12. በከተማ ግብርና ዘርፍ ንግድ ፈቃድ ለማውጣት የሚያስፈልጉ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችና ስለሚሟሉበት ሁኔታ ግንዛቤ መስጠት፣

13. የከተማ ግብርና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ድጋፍ እንዲያገኙ የግንዛቤ ማስጨበጫ አገልግሎት መስጠት፤
14. መስሪያ ቦታዎች ተጠቃሚ የሚሆኑትን ኢንተርፕራይዞች አስፈላጊ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ምክር አገልግሎት መስጠት፡፡

## 7. የምዝገባና መረጃ አገልግሎት መስጠት

1. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የሚሰጡ አገልግሎቶችንና አገልግሎቶችን ለማግኘት ባለጉዳዮች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶችና የአሰራር ቅደም ተከተሎች መረጃ መስጠት፤
2. ስራ ፈላጊ ነዋሪዎችን በባህር መዝገብ በመመዝገብ የስራ ፈላጊ መለያ መታወቂያ ካርድ መስጠት እና የተመዘገቡትን ስራ ፈላጊዎችን በዘመናዊ የመረጃ ቋት ማስገባት፤
3. በአንድ ማዕከል ከተደራጁ ሥራ ፈላጊዎች መካከል በየደረጃው የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን የወሰዱትን የሥራ ፈላጊነት መታወቂያ ካርድ እንዲመልሱ ለማድረግ፤
4. ወደ ሥራ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ተገልጋዮች የሥራ ዕድል አማራጮችን እና ቅድመ ሁኔታዎችን የማመቻቸት አገልግሎት መስጠት፤
5. ወደ ሥራ ለመሰማራት ህጋዊ የአደረጃጀት አማራጮች እና የመንግስት የድጋፍ ማዕቀፎች እንዳሉ መረጃ መስጠት፤
6. በገበያ አዋጪና ተፈላጊ የሆኑትን የስራ መስኮች፣ የስልጠና አይነት፣ የቆይታ ጊዜና ቦታ መረጃ መስጠት፤
7. የገበያ ትስስር ጥያቄ መቀበል፣ የገበያ ጥናት መረጃ መስጠት፤
8. በተለያዩ ምክንያት ጥገናና እድሳት የሚያስፈልጋቸው የመስሪያ ቦታዎች ጥገናና ዕድሳት አገልግሎት ለማግኘት የሚቀርብ ጥያቄ መቀበል ፤
9. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እና ሰርተፍኬት አወጣጥ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን መስጠት፤
10. የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አወጣጥ መረጃዎችን መስጠት፤
11. የንግድ ነክ መረጃ መስጠት፤
12. የከተማ ግብርና ነክ መረጃ መስጠት፤

13. ተገልጋዮች በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጅ በመጠቀም አገልግሎቶችን ማግኘት የሚችሉበትን መረጃ መስጠት፡፡

## 8. ለስራ ዝግጁ የሚያድረግ የአንድ ማዕከል አገልግሎት

1. የነዋሪነት ምዝገባ ማረጋገጫ ቁጥር መስጠት፣
2. ቋሚ የሥራ አጦች መዝገብ ማቋቋም፤
3. ሥራ ፈላጊዎችን መመዝገብ፤
4. የስራ አጥነት ካርድ መስጠት፤
5. ስራ ፈላጊዎችን በሚፈልጉት የአደረጃጀት ዓይነት ማደራጀት፣
6. የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳዳሪያ ደንብ ረቂቅ ሰነድ እና ቅፃቅፆች ናሙና መስጠት፣
7. በህብረት ሽርክና ማህበር እና በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሚደራጁ እና ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ የድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣
8. በህብረት ሽርክና ማህበር እና በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ እንዲጸድቅ የማመቻቸት አገልግሎት መስጠት፣
9. በህብረት ሽርክና ማህበር እና በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሚደራጁ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ የውሳኔ ሃሳቦች ማሻሻያዎች ሙያዊ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣
10. በህብረት ሽርክና ማህበር እና በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሚደራጁ እና ለተደራጁ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቃለ ጉባኤ እንዲጸደቅ የማመቻቸት ድጋፍ አገልግሎት መስጠት ፣
11. በጣት አሻራ የተደገፈ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እና ሰርቲፊኬት መስጠት፣
12. የንግድ ምዝገባ አገልግሎት መስጠት፤
13. የንግድ ስያሜ መስጠት፤
14. የንግድ የድርጅት ስም መስጠት፣
15. አዲስ የንግድ ስራ ፈቃድ መስጠት፡፡

9. <u>የድጋፍ አገልግሎት መስጠት</u>

1. አዋጪ የቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ድጋፍ መስጠት ፣
2. ለጀማሪ ኢንተርፕራይዞች የእድገት ደረጃ ማሳወቂያ ምስክር ወረቀት መስጠት ፣
3. የክህሎት ስልጠና ድጋፍ ማመቻቸት፤
4. የመሥሪያ ቦታ ኪራይ ውል የማዋዋል እና የማደስ አገልግሎት መስጠት፤
5. የብቃት ማረጋገጫና ምዘና ማዕከሉ ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የላከውን ተመዝነው ብቁ የሆኑትን ሰልጣኞች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለባለጉዳዮች መስጠት፣
6. የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ አገልግሎት መስጠት፣
7. ብድር መስጠት፤ቁጠባ እንዲቆጥቡ ማድረግ ፣ ብድር ማስመለስ ፣
8. የካፒታል መሳሪያዎች አቅርቦት ማመቻቸት
9. የዘርፍ ለውጥ፣ ካፒታል ማሻሻያ፣ የስም ለውጥ፣ አድራሻ ለውጥ እና የስራ አስኪያጅ ለውጥ ማድረግ፤
10. የንግድ ፈቃድ ማስመለስ አገልግሎት ድጋፍ መስጠት፣
11. የንግድ ምዝገባ ስረዛ ማድረግ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አገልግሎቶችን በውክልና የሚሰጡ መሥሪያ ቤቶች እና ውክልና የሚሰጡባቸው አገልግሎቶች</u>

10. <u>ስለ ውክልና</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 ለእያንዳዱ አስፈጻሚ ተቋማት የተሰጠው ሥልጣንና ተግባ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የሚሰጡ አገልግሎቶችን አስፈጻሚ ተቋማቱ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (15) መሠረት በአንድ ማዕከል ሊሰሩ የሚገባቸውን ሥራዎች ለቢሮው በውክልና እንዲሰጡ የጋራ ስምምነት ይደረጋል፡፡

11. <u>ውክልና የሚሰጡ የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቤቶች</u>

1. የአስተዳደሩ ገቢዎች ቢሮ፤
2. የአስተዳደሩ ንግድ ቢሮ፤
3. የአስተዳደሩ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠናና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፤
4. የአስተዳደሩ የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን፤
5. የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፡፡
6. የአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም፤
7. የአዲስ ካፒታል ዕቃዎች ፋይናንስ አክሲዮን ማህበር፣

12. <u>የገቢዎች ቢሮ</u>

1. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ሰርተፍኬት ለሚያወጡ የጣት አሻራ መቀበል፤
2. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ሰርተፍኬት መስጠት፤
3. የደረሰኝ ህትመት ፍቃድ አገልግሎት መስጠት፡፡

13. <u>ንግድ ቢሮ</u>

1. አዲስ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለሚደራጁ ለግል ፣ ለህብረት ሽርክና ማህበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ለመስጠት፤
2. አዲስ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንርፕራይዞች ለሚደራጁ ለግል፣ ለህብረት ሽርክና ማህበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ማህበራት / የድርጅት ስም ስያሜ ለመስጠት፤
3. አዲስ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንርፕራይዞች ለሚደራጁ ለግል ፣ ለህብረት ሽርክና ማህበር ፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ስም ስያሜ መስጠት፤
4. አዲስ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንርፕራይዞች ለሚደራጁ ለግል፣ ለህብረት ሽርክና ማህበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አዲስ የንግድ ስራ ፈቃድ ለመስጠት፡፡

14. <u>ቴክኒክና ሙያ ሥልጠናን ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ</u>

1. ሥልጠና ለሚያስፈልጋቸው ሥራ ፈላጊዎች እና ኢንተርፕራይዞች የሚመለመሉበትን መሥፈርትና የሚሰጠውን አገልግሎት ዓይነት ማሳወቅ፤
2. ሥልጠናው የሚሰጥበትን ቦታ ፣ ወቅት ፣ ዘርፍ እና ዓይነት የማሳወቅ፡፡

15. <u>የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን፤</u>

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ለሚደራጁ ሥራ ፈላጊ ሰልጣኞችን መዝኖ ብቁ የሆኑትን የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ ሰርቲፍኬት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ውስጥ ለመስጠት፡፡

16. <u>የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ</u>

ለሥራ ፈላጊዎች የነዋሪነት ምዝገባ ማረጋገጫ ቁጥር መስጠት አለበት፡፡

17. <u>አዲስ ካፒታል ዕቃዎች ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበር</u>

1. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ኢንዱስትሪዎች የሚቀርብ የካፒታል ዕቃዎች ለማግኘት የሚያስፈልጉ መሥፈርቶች ዝግጅትና ተጠቃሚነታቸውን ማመቻቸት፤
2. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ኢንዱስትሪዎች የጥገና አገልግሎት የሚሰጥበትን ሙሉ መረጃ መስጠት፡፡

18. <u>የአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም</u>

በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ለሥራ ፈላጊዎችና ኢንተርፕራይዞች የብድር አገልግሎት ለመስጠት፣ ቁጠባ ለመቀበልና ብድር ለማስመለስ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ በቋሚነት በመመደብ አገልግሎት መስጠት፡፡

19. <u>የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ</u>

ለሥራ ፈላጊዎችና ኢንተርፕራይዞች አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች አቅራቢያ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በመክፈት አገልግሎት መስጠት፡፡

## ክፍል ስድስት

## በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የመሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት እና ተግባር

20. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንናተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያውን የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጠፋ ለማድረግ የስራ ፍሰቱን ቅደም ተከተል በጠበቀ ሁኔታ የፈፃሚዎችን የቦታ አቀማመጥ በማስተካከል አገልግሎት መስጠት፤
2. ተገልጋዮች ሁሉንም ዓይነት አገልግሎቶች በአንድ የአገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ብቻ እንዲጠቀሙ በሚያስችል መልኩ እንዲቀረጽና ተገልጋዮች በቅፁ መሰረት እንዲጠቀሙ ማድረግ፤
3. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች አቀራረብ እና አፈታት ሂደት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ በቅድሚያ ታይቶ የሚፈታበትን ስልት መዘርጋት፤
4. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አገልግሎትን ለመስጠት መስሪያ ቤቶች ውክልና የሰጡባቸውን አገልግሎቶች ህጉና ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት መስጠት፤
5. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ ውክልና የተሰጡትን አገልግሎቶች በተሰጠው ውክልና መሰረት ለየተቋማቱ ወርሃዊ ሪፖርት ማቅረብ፤
6. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ እንደ አስፈላጊነቱ በወረዳው ውስጥ ከአንድ ጣቢያ በላይ በማቋቋም አገልግሎት መስጠት፤
7. የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚያስችሉ የአሰራር፣ የአደረጃጀት፣ የመመሪያና የስራ ማንዋል ማሻሻያ ጥናት በማድረግ መተግበር፤
8. የአንድ ማዕከል አገልግሎቱን ለመስጠት በመረጃ ቋት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ስርዓት የተደገፉ አገልገሎቶች ለመስጠት የሚያስችል አሰራር የመዘርጋትና መተግበር አለበት፡፡

9. አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ውስጥ ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የመለየትና ሟሟላት፤
10. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በተሟላ መልኩ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ በበጀትና ቁሳቁስ መደገፍ፤
11. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ውስጥ የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የመረጃ ማሰራጫና የአገልግሎት አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ ቢል ቦርዶች፣ ባነሮች፣ ብሮሸሮች፣ በራሪ ወረቀቶች እንዲዘጋጁ ማድረግ፤
12. በአንድ ማዕከል አገልግሎት የሚሰጡ አገልግሎቶችን መሠረት ያደረገ የተሻለ ልምድና ትምህርት ዝግጅት ያላቸው የአንድ ማዕከል ፈፃሚዎችን ቅጥር መፈፀምና ማስተዳደር፤
13. የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሰጭ ባለሙያ ምደባ እንደ አንድ ማዕከሉ አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የስራ ስፋት፣ የተገልጋይ ብዛትና የኢንተርፕራይዞች ብዛት ታሳቢ ያደረገ የሰው ኃይል ማሟላት፤
14. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የተመደቡ ባለሙያዎች ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ እና በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ስራ ማሰማራት፤
15. ቀደም ሲል የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል ቀጥረው በማዕከሉ አስገብተው ሲያሰሯቸው የነበሩትን ፈጻሚዎች ተረክቦ ማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፡፡

## 21. <u>ውክልና የሰጡ መሥርያ ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ውክልና መስጠት ፤
2. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች የተሟላ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር አስፈላጊ መረጃዎች ተደራጅተውና ተተንትነዉ ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ለአገልግሎት እንዲውሉ ማመቻቸት ፤

3. የባለድርሻ አካላት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች አገልግሎት አሰጣጥ በሰጡት ውክልና መሰረት እና በዜጎች ስምምነት ቻርተር መሰረት መስፈርቶች ተጠበቀው እንዲሰሩ መደገፍ፤
4. አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ መስፈርቶችን በየጊዜው ማሻሻያ የተደረገባቸውን ጉዳዮች ማሳወቅ፤
5. የተሻሻለ አገልግሎት ለመስጠት፣ የመረጃ ጥራትና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ሶፍትዌሮችን እና የመረጃ ቋቶቹን ጨምሮ የተቀናጀ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ተግባራትን ከቢሮው ጋር በጋራ የመሥራት ፣ ማሟላትና ማመቻቸት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 22. <u>የከንቲባ ጽህፈት ቤት</u>

1. ለስራ ፈላጊዎችና፣ ለኢንተርፕራይዞች እና ለኢንዱስትሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ ተጠሪነታቸው ለፌደራል የሆኑ ተቋማት አገልግሎታቸውን ተደራሽ ለማድረግ በከተማ አስተዳደሩ ሁሉም ወረዳዎች በሚቋቋሙት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የተሟላ አገልግሎት በአንድ ስፍራ ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀት፣ አሰራርና ህጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ያስተባብራል፤
2. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ለሰራ ፈላጊዎችና ለኢንተርፕራይዞች፣ ለኢንዱስትሪዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ከተጠቀሱት ተቋማት ውጭ እንደ አስፈላጊነቱ እየታየ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊወስን ይችላል፡፡

## 23. <u>ስለስብሰባ ጊዜና የሪፖርት አቀራረብ</u>

1. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ እንዲሰጡ በውክልና የተሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ ቢሮው ለየተቋማቱ በየወሩ ሪፖርት ያደርጋል፤
2. ቢሮው ውክልና ከሰጡት ተቋማት ጋር በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ስብሰባ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡን ሂደት ይገመግማሉ፤
3. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) እንደተጠበቁ ሆኖ ቢሮው እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊጠራ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**24. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**25. ስለተጠያቂነት**

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሶ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**26. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች**

1. የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 75/2014 ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፤
2. ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ቢሮው ያወጣቸው ማንኛውም መመሪያዎች እና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**27. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ቢሮው ይህን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**28. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ቁጥር ከመጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም**

**ጃንጥራር ዓባይ ይግዛው**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የስራ፣ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ**